# አገር እንዴት ሰነበተች ቁጥር 41

ህዳር 18 ቀን 2015ዓም(27-11-2022)

በዚህ በያዝነው የህዳር ወር ሁለተኛ ሳምንት የአገር እንዴት ሰነበተች ስርጭታችን በአገራችን በኢትዮጵያ የተከሰቱትን ሁኔታዋች ለመተንተን መነሻ ያደረግነው በራሱ በህዳር ወር ታሪካዊ ገጠመኞች ይሆናል።

በቅድሚያ ግን ስለጊዜ ቅምር ማንሳቱን መርጠናል።ጊዜ በዘመን፣በዓመት፣በወር፣በሳምንት፣በቀን፣በሰዓት፣በደቂቃና በሴኮንድ ይሰፈራል።እያንዳንዱ የጊዜ ክፍል የሚለካበት መጠንና እርዝማኔ አለው። ከዚያም ባሻገር ተለይቶ የሚታወቅበት ገጠመኞች ይኖሩታል።በዚህ ዘመን ወይም በዚህ ዓመት፣በዚህ ወር ወይም በዚህ ሳምንት፣በዚህ ቀን ወይም በዚህ ሰዓት ይህ ሆነ፣ተደረገ የሚለው ለወቅቱ ተጨማሪ መለያ ነው።ድርጊቶች ወይም ክስተቶች ከዘመኑና ፣ከዓመቱ፣ ከወሩና ከሳምንቱ፣ከቀኑና ከሰዓቱ ብሎም ከደቂቃዎች ጋር የተሳሰሩ ናቸው።የታሪክም ሰነድ የሚዘጋጀው ይህንኑ የጊዜ ቅምር ተከትሎ ነው።ብዙ ዘመናትን፣ዓመታትንና ወራትን፣ሳምንታትንና ቀናትን ከተሸከሙት የታሪክ መታወቂያቸው ጋር በአንድ ጥራዝ መተንተንና ማቅረብ አይቻልም፤ቢቻልም የብዙ ጥራዞች ሥራን ይጠይቅ ነበር።እድሜ ለሳይንስ አሁን ላይ ይህ በቀላል መንገድ የሚመዘገብበት ዕድል ተፈጥሯል።ጥንት በወረቀት ላይ የሰፈሩ ማስረጃዎችና የታሪክ ሰነዶች አሁን በኮምፒውተር ሳጥን ውስጥ ተሰብስበው (ዲጂታላይዝድ ሆነው) ለትውልድ ሊተላለፉ ችለዋል።

ጊዜ ማለቂያና መቆሚያም ስለሌለው ታሪክም እንዲሁ አይቆምም፣ አዳዲስ ታሪኮችና ክስተቶችን እዬመዘገበ ይጓዛል። ስለጊዜ በጥቂቱ ይህንን ካልን ዘንዳ የጊዜ አካል ስለሆነው ስላለንበት የህዳር ወር በታሪክ ያለውን ቦታ በትንሹ ማቅረብ እንወዳለን።

የሕዳር ወር በአገራችን ታሪክ ብዙ ክስተቶችን ያዬንበትና አሁንም እያዬን ያለንበት ወር ነው።ወደ ጥንቱ የህዳር ወር የታሪክን መዝገብ ገልጸን ስናዬ ከ114 ዓመት በፊት የመጀመሪያውን የዓለም ጦርነት ተከትሎ በተከሰተው ድንበር ተሻጋሪ የጉንፋን(ኢንፍሉዌንዛ)በሽታ ከ100 ሚሊዮን ሕዝብ በላይ በሞት የረገፈ ሲሆን፣ በአገራችንም ከ50 ሽህ ሰው በላይ ለሞት ተዳርጓል።በዚህ ወረርሽኝ የአገሪቱ ባለሥልጣኖች ሳይቀሩ ተለክፈው አብዛኛዎቹ ሲሞቱ ሌሎቹ ለመትረፍ ችለዋል።ይህ የአንደኛውን ዓለም ጦርነትን ተከትሎ የመጣው ወረርሽኝ በወታደራዊው እንቅስቃሴ ጋር በፍጥነት ሊዛመት የቻለ ሲሆን በደረሰው የኤኮኖሚና የመዋቅር ስብራት፣የአዬር መበከልና የቁሻሻ ክምር በቀላሉ ለበሽታው (ለቫይረሱ) መራባት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል።ይህንን በሽታ ለመቋቋም የነበረው መድሃኒትና የሕክምና አገልግሎት በጣም ውስን ስለነበር የከበርቴ ወይም ታላላቅ አገሮችም እንኳን ቢሆኑ ሊቋቋሙት አልቻሉም።በተለይም በጭርንቁስ ኑሮ ውስጥ የሚማቅቀው የሠራተኛው ክፍል የዚያ ሰለባ ከመሆን አላመለጠም።በጦርነቱ ከረገፈው በላይ በዚህ ወረርሽኝ የሞተው እንደሚበልጥ በታሪክ ተመዝግቧል።በጦርነቱ ሞቷል የተባለው ቁጥሩ ከ50 ሚሊዮን እንደማይበልጥ ይነገራል።

ይህንን በሽታ የአገራችን ሕዝብ የህዳር በሽታ የሚል ስያሜ ሰጥቶታል።ምክንያቱም የተነሳበት ወር ህዳር በመሆኑ ነበር።ለዚህ ተዛማች በሽታ አገራችን ለመቋቋም የሚያስችል የዘመናዊ ህክምና ተቋምና መድሃኒት ባይኖራትም የሕዝቡና የመሪዎቹ ብልህነት የፈጠረው የመከላከያ ዘዴ ነበር ።ዘዴውም በሽታው ከቁሻሻ ጋር የተያያዘ በመሆኑ አዬሩ ሊበከል መቻሉን በመገንዘብ መስፋፋቱን ለማቆም በከተማና በገጠር የሚኖረው ሕዝብ እሳት እያነደደ ከባቢውን በጭስ እንዲያጥን የወጣው ትዕዛዝና

መመሪያ ነበር።በዚህ መመሪያ መሠረት ሕዝቡ እሳት በማንደድ የወረርሽኙን ፍጥነት ሊገታው ችሏል። ከዚያም ሂደት ጋር በማያያዝ እስከ አሁን ድረስ የሕዳር ወር የማጠንት ወር ሊባል ችሏል።ለጉዳይ ቀጠሮም ለመያዝ ህዳር ከመታጠኑ በፊት ወይም ከታጠነ በኋላ የሚል የጊዜ መግለጫ መጥቀሱ የተለመደ ሆኗል።

የህዳርን ወር ስናነሳ በዚህ የወረርሽኝ ወቅት ብቻ የሚገታ አይደለም ።አገራችን ባሳለፈቻቸው ብዙ የህዳር ወራት መጥፎና መልካም ክስተቶችን ተቀብላበታለች።ከመጥፎ ክስተቶቹ መካከል የዛሬ 62 ዓመት የተካሄደው የመንግሥት ግልበጣ ሙከራና ብዙ ባለሥልጣኖች ካለፍርድ የተገደሉበት የ1953 ዓም የታህሳሱ ድርጊት የተጠነሰሰው በህዳር ወር ውስጥ ነበር። ከዚያም በኋላ በ1965 ዓም በውጭ ጉዳይ ሚንስትሩ በአቶ ከተማ ይፍሩ ውክልና የተቀናጀው የለውጥ ሃይል ለንጉሠ ነገሥቱ ያቀረበው ጥያቄ በዚህ በህዳር ወር ነበር። ንጉሥ አጼ ሃይለሥላሴ በየአመቱ ለህዳር ጾም ድሬዳዋ ከተማ በሚገኙበት ጊዜ ነበር።አቶ ከተማና ቡድናቸው የንጉሡን ዕድሜ መግፋት ከግምት ውስጥ በማስገባትና የ80ኛው የልደት በዓላቸው በአፍሪካ ደረጃ መከበሩን እንደ ትልቅ ክብረወሰን በመቁጠር ሥልጣናቸውን ለአልጋወራሻቸው አስረክበው ዘውዳዊው ሥርዓትም እንደ አውሮፓውያን አገሮች ማለትም እንግሊዝ፣ሆላንድና ስዊድን በሕጋዊ ሥር የዋለ (Constitutional Monarchy)እንዲሆን የሚጠይቅ ነበር።ንጉሠነገሥቱ ግን ይህንን ሃሳብ እሳት ለብሰው እሳት ጎርሰው ውድቅ ከማድረጋቸውም በላይ ጠ/ ሚኒስትር አቶ አክሊሉ ሃብተወልድን ድሬዳዋ ድረስ በአስቸኳይ ጠርተው አቶ ከተማ ይፍሩ እንዲታሰሩ አዘዙ።ጠ/ሚኒስትሩ ግን ሊያስከትል የሚችለውን የፖለቲካ ቀውስና አቶ ከተማ ይፍሩ ካበረከቱት መልካም ሥራ ጋር ታይቶ በሌላ መንገድ ቢሆን ይሻላል በማለታቸውና ንጉሡን በማሳመናቸው ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነት ተነስተው የንግድ ሚኒስትር እንዲሆኑ አስደረጉ።አቶ ከተማ ይፍሩም በዚህ በአዲሱ ሹመታቸው ማግስት የዳቦ ዋጋ እንዲቀነስ ደንብ አወጡ፤በዚህም በሕዝቡና በተለይም በተማሪው ዘንድ ከፍተኛ ድጋፍ ለማግኘት ቻሉ።ንጉሠ ነገሥቱ ዬቀረበላቸውን ምክር ቢቀበሉ ኖሮ ታፍረውና ተከብረው በኖሩ፣ በታሪክም ትልቅ ቦታ ይዘው ፣አገራችንም ወደተሻለ አቅጣጫ ባመራች ነበር።መሪዎች ለአገርና ለራሳቸውም የሚበጀውን ምክር ሳይቀበሉ ከንቱ ቀርተው አገርን ለመከራ የዳረጉ ንጉሥ ሃይለሥላሴ ብቻ አይደሉም።ከሳቸውም በኋላ የመጡት አምባ ገነኖች ያንኑ መንገድ ተከትለዋል፤የአሁኖቹም የሕዝቡን ጥሪና ጥያቄ አንቀበልም ስላሉ በተለይም የጎሳ ፖለቲካ ተሸካሚዎች ስለሆኑ መጨረሻቸው ካለፉት አምባገነኖች የከፋ ይሆናል።መውደቃቸው ስለማይቀር ሲወድቁ አገር ይዘው እንዳይወድቁ ሕዝቡ ጠንካራ ግንብ መገንባት አለበት።

የዛሬ 48 ዓመት በ1967 ዓም የደናቁርቱ የአምባገነን ወታደሮች አገዛዝ ወይም ደርግ፣እንደመንግሥቱ ሃ/ማርያም አይነቶቹ በምቀኝነትና በበታችነት ስሜትና በቀል ባበዱ ሰዎች ተመርቶ በዜጎች ላይ የፈጸመው ፍርድ አልባና ኢሰብአዊ ጭፍጨፋ የተከናወነውም በህዳር ወር በ14ኛው ቀን ላይ ነበር። ይህንን የጭካኔ እርምጃ ተከትሎ እስከአሁኑ ድረስ እስከ2015 ዓም ህዳር ወር የዘለቀ መከራ በአገራችንና በሕዝቧ ላይ ሲፈጸም ኖሯል፤እዬተፈጸመም ነው።

ከ114 ዓመት በፊት ከተከሰተው የጉንፋን ወረርሽኝ ጋር የሚመሳሰለው ከሃምሳ ዓመት ወዲህ የተንሰራፋው የፖለቲካ ወረርሽኝ የብዙ ዜጎችን ሕይወት ቀጥፏል፤ እዬቀጠፈም ነው።ከ114ቱ ዓመት በፊት ከተከሰተው ወረርሽኝ የባሰ የሚያደርገው እንደዛ ጊዜው መድሃኒት አለመገኘቱ ነው።ከዳር እስከዳር ሕዝቡንም፣ አዬሩንም መሬቱንም ለበከለው የጎሳ ወረርሽኝ መድሃኒት ለማግኘት በማዳገቱ ሲሆን እንደዛ ጊዜው ጠንካራ አገር ወዳድ መሪ ባለመኖሩ ሕዝብ ተናቦና ተደማምጦ በከተማና በገጠር የፖለቲካ ወረርሽኙን በለውጥ ነበልባል (እሳት) ለማሶገድ ጠንካራ ሕዝባዊ መፍትሔ አለመገኘቱ ነው።ይባስ ብሎ ሕዝቡ የፖለቲካው ወረርሽኝ ተሸካሚና አዛማች መሆኑ የመፍትሔ ፍለጋውን ከባድ

አድርጎታል።ይህ የሆነው የፖለቲካ ወረርሽኙ በጎሳ መልክ የሚታደል ቫይረስ በመሆኑ ሲሆን ያንን እዬተቀበለ ለመተላለቅ መሰለፉ በሽታውን ከማሶገድ ይልቅ እንዲባዛ እረድቶታል።ከሁለት ዓመት በፊት በ2013 ዓም በጥቅምት ወር መጨረሻ ሳምንት በትግራይ ተጀምሮ በህዳር ወር የተከዜን ድንበር አልፎ የተቀጣጠለው ጦርነት ኢሕአዴግ የተባለው ቡድን አባላት በሆኑት በህወሃትና በኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና መካከል ጥቅምና ስልጣን የጫረው ጦርነት ነበር፤በዚህም ጦርነት የብዙ ዜጎች ህይወትና ንብረት ጠፍቷል።አሁንም ወያኔና ግብረአበሮቹ የአማራውና የኤርትራ የታጠቀ ሃይል ከትግራይ ይውጣ በሚለው አቋማቸው ጸንተው ትጥቅ ላለመፍታት ምክንያት አድርገውታል።ለአራተኛ ዙር ጦርነትም እዬተዘጋጁ ነው።እውነቱ ይህ ሆኖ ሳለ የአብይ አህመድ ኦሕዴድ ብልጽግና ጣቱን የቀሰረውና ለማጥቃትም የሮጠው ለሙብቱ በሚታገለው በአማራው ላይ ብቻ ነው።ከራሱ አጽመእርስት ለቆ እንዲወጣና ቦታውን ለወያኔ ለማስረከብ የበገባውን ድብቅ ስምምነት ለማስፈጸም ሃይሉን በመጠቀም ላይ ይገኛል።ከኤርትራ ጋር ያለውን ጉዳይ እንዴት እንደሚፈታው ግራ ገብቶታል።ኢሳያስ አፈወርቂ ምን ምላሽ እንደሚሰጥም አልታወቀም።በቀላሉ ለአሜሪካ መራሹ የአውሮፓውያንና ለወያኔዎቹ ጥያቄ ይንበረከካል ተብሎ አይታሰብም።ወያኔ ከቦታው መመለሱ ለኤርትራ በተለይም ለኢሳያስ አፈወርቂ ህልውና ስጋትና እራስ ምታት እንጂ ሰላም እንደማይፈጥር የታወቀ ነው። ወያኔ ከኤርትራ ተቃዋሚ ሃይሎች ጋር ጥምረት ፈጥሮ እንደሚንቀሳቀስ አይካድም። ምናልባትም ነገሩ ከተካረረ የአማራው ትግል ከኤርትራ በኩል መንግሥታዊ ድጋፍ ለማግኘት የጥቅም ሽርክና ወይም አጋርነት ሳይፈጥር አይቀርም። በቀጣዩ የምናዬው ይሆናል። በቅድሚያ ግን የሚኖረውን ጥቅምና ጉዳት መመርመሩና አቋም መያዙ ተገቢ ነው።

ከብዙ እልቂትና ውድመት በኋላ አሁን ከወር በፊት በጥቅምት ወር ተጀምሮ በያዝነው በዚሁ በህዳር ወር መግቢያ ላይ እነዚህ አገር አጥፊ ቡድኖች የደረሱበት ስምምነት ለቀጣዩ መከራ ቃል ኪዳን የገቡበት ውል መሆኑን እያዬነው ነው። ካለፉት ዓመታትና ወራቶች ጀምሮ እስከአሁኑ የህዳር ወር ድረስ የሕዝብ ደም መፍሰስና መፈናቀል እንደቀጠለ ነው።በተለይም በአማራው ማህበረሰብ ላይ የሚደርሰው ጥቃት ይበልጥ ጨመረ እንጂ እዬቀነሰ አልመጣም።በስምምነታቸው መሰረት የወልቃይትና ጠገዴን እንዲሁም የራያና አዘቦን ለም መሬት ከአማራው ቀምቶ ትግራይን የመገንጠሉ ፋይል አልተዘጋም።ይህንን እቅድ ለማሳካት በአብይ አህመድ ግልጽ ተባባሪነት የአማራውን የታጠቀ ሃይል ፋኖንና ልዩ ሃይሉን ትጥቅ በማስፈታትና ከቦታው በማሶጣት ላይ ተሰማርቷል። ብዙዎቹን አስሯል፤ ሌሎቹንም መሳሪያ መታጠቅ እንደማይችሉ በሕግ ደንግጓል።ወያኔም ጦሩን አሰልፎ ለዳግም ወረራ በዝግጅት ላይ ነው።በአንዳንድ ቦታዎችም ግልጽ ጦርነት አካሂዷል።ለአራተኛ ጊዜ ሙሉ ጦርነት ውስጥ ላለመግባቱ ዋስትና የለም። በውጭ የሚነዛው የፕሮፓጋንዳው ዘመቻ የሚያመለክተውም ይህንኑ ነው። ይህ በእንዲህ እያለ በደቡብና ደቡብ ምዕራብ በተለይም በኦሮሚያ ክልል በወለጋ ክ/ሃገር በኦነግና በኦሕዴድ ጥምር ሃይል የሚካሄደው የንጹሃን ጭፍጨፋ በዬዕለቱ ጨምሯል። ወንጀለኞች በንጹሃን ጭፍጨፋ ሃይላቸውን በማሳዬት እውቅና አግኝተው ለድርድር የሚቀርቡበትና የሥልጣን ተቋዳሽ የሚሆኑበት ተግባር ሆኗል።ግፍና መከራው ሲበዛበት እራሱን ለመከላከል የአማራው ማህበረሰብ የሚያደርገው እንቅስቃሴ ብርክ የለቀቀባቸው ጸረ አንድነትና ጸረ ኢትዮጵያ የሆኑ ቡድኖች፣ ጨፍጫፊውን የኦነግ አሸባሪ ስብስብ ከወንጀለኛነት ተራ አውጥተው እንደሕዝባዊ የፖለቲካ ሃይል አድርገው የፈጸመውንና በመፈጸም ላይ ያለውን ኢሰብአዊ ድርጊት ሳይኮንኑ በመሸፋፈን በድርድር እንዲሳተፍ ጥሪ ሲያደርጉ ተደምጠዋል።ከነዚህ መካከል በቀጥታና በተዘዋዋሪ የወንጀሉ ተካፋይ የሆነው በነጁዋርና በቀለ ገርባ እንዲሁም በአስመሳዩ መራራ ጉዴና የሚመራው የኦሮሞ ፌዴራሊስት ፓርቲ አንዱ ነው።ይህ ፓርቲ በዚህም በዚያም ብሎ ከብልጽግና ቡድን ጋር ያለውን የሥልጣን ሽኩቻ አሶግዶ ኦሮሚያ የሚሉትን አገር ለመመሥረት በሚያስችለው ደረጃ ላይ ለመሳተፍ እንጂ ለኦሮሞ ሕዝብ አስበው እንዳልሆነ በወለጋ ፣በሆሩጉድሩና በቄለም ወረዳዎች፣በሰሜን ሸዋ በሚደግፉት ኦነግ

ከአማራው ጋር የሚጨፈጨፈው የኦሮሞ ደሃ ሕዝብ አያሳስባቸውም። የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታይ ከሆነ በባሰ ደረጃ የሚያጠቁት ሆኗል።በግለሰብም ደረጃ ድርጊቱን የሚቃወም የኦሮሞ ተወላጅ ካለ ለነሱ ባንዳና ጎበና ነው። አብይ አህመድ ኦሮሞ ኦሮሞን አይገድልም ይበል እንጂ በገሃድ በኦሮሞነቱ አልዳነም።በደቡብም ቢሆን በተመሳሳይ ደረጃ የጉራጌው ማህበረሰብ ተወላጆች በሚያቀርቡት የመብት ጥያቄ የተነሳ እዬታፈኑና እዬታፈሱ በዬእስር ቤቱ ስቃይ በመቀበል ላይ መሆናቸው ያደባባይ ሚስጥር ነው።ለዚያም የጉራጌ ህዝብ በአደባባይ ወጥቶ የፍትሕ ያለህ እያለ ይጮሃል።እኛም ይህ የኦሮሙማውና የተከታዮቹ እርምጃ በአማራው ላይ ብቻ ያነጣጠረ ሳይሆን በሌሎቹም ማህበረሰቦችም ላይ የሚደርሰው ግፍና መከራ ኢትዮጵያን ከማፈራረሱ ደባ ጋር የተቆራኘ የወያኔና የኦነግ፣ኦሕዴድ ብልጽግና ጥምር ዓላማ መሆኑን ከዚህ የበለጠ ማስረጃ አይኖርም፤ስለሆነም በጋራ ዘመቻ ከፍቶ የሚያጠቃቸውን ጸረ ኢትዮጵያና ኢሰብአዊ ቡድን በጋራ ተሰልፈው ሊፋለሙት ይገባል፣በተናጠል መጮህና መታገል ያስጠቃል እንጂ ውጤት አያመጣምና ተባበሩ እንላለን።

ይህንን ተከትሎ በዚሁ በያዝነው ህዳር ወር ከቀናት በፊት መጨፍጨፍ ያስመረረው በወለጋ ክ/ሃገር በተለያዩ ቦታዎች የሚኖረው የአማራው ተወላጅ ብሞትም ታግዬ ልሙት በሚል ውሳኔ እራሱን አደራጅቶ የኦነግንና ተባባሪዎቹን ጨፍጫፊ ሃይል ከመመከት አልፎ ድባቅ እዬመታ ይገኛል።ይህም እርምጃ በሁሉም የኦሮሙማ ቡድኖች ዘንድ ብልጽግናን ጨምሮ ብርክ አስይዟል።ለመቋቋምም ያለ የሌለ ሃይላቸውን በነሱ የሚመራውን የፌዴራል ወታደር ሳይቀር በአማራዎቹ ላይ አዝምተማል።አሁን የሞት የሽረት ትግሉ ተቀጣጥሏል።በህዳር 13 ቀንም የአማራ ፋኖ አንድነት መፍጠሩን ይፋ አድርጎ መግለጫ አውጥቷል። ይህንን የለውጥ ሂደት ለብዙ ጊዜ ስንጠይቀው የነበረ በመሆኑ ውሳኔውን ተቀብለናል።በውጭ አገር የሚንቀሳቀሰው የአማራው መብት ተከራካሪ እንደ ጉልት ገበያ ለዬብቻው መንቀሳቀሱን ትቶ በአንድ የጋራ መድረክ በመሰባሰብ ድጋፉን ለተቋቋመው የፋኖ ግንባር እንዲያበረክት ጥሪ እናደርጋለን።የፋኖ ተጋድሎ ለአማራው ብቻ ሳይሆን፤ለሁሉም ኢትዮጵያዊ ያገር ባለቤትነትና የዜግነት መብት፣ለእኩልነትና ለፍትሕ ስለሆነ ሌሎቹንም በኢትዮጵያዊነታቸው የሚያምኑና የጎሳ ፖለቲካውን የሚቃወሙ የማህበረሰብ ተወላጆች ለማሰለፍ ሰፊ ብሔራዊ መድረክ እንዲፈጠር ጥሪ እናደርጋለን።

ኦነግ በጫካ ሰላማዊ ዜጎችን በማገት፣ ኦሕዴድ ብልጽግና በከተማ ያውም በሕግ ተቋማት በሆኑ ፍርድ ቤቶች እዬተናበቡ የገንዘብ ዘረፋውን ተያይዘውታል።በተለይም አማራውን በሞራልም በኤኮኖሚም እንዳያንሰራራ ተባብረው እያደቀቁት ነው።ከዚሁ ከፍርድ ቤት የችሎት የወንጀል ተግባር ሳንወጣ አንጋፋው ጋዜጠኛና የታሪክ ተመራማሪው ታዴዎስ ታንቱ በቀጠሮ ጋጋታ እዬታሸ ብዙ ወራት አሳልፏል።ሰሞኑንም ፍርድ ቤት ቢቀርብ ዳኛ የለም በሚል ሰበብ ወደ እስር ቤት እንዲመለስ ተደርጓል። ፍርድ ቤትን የበቀል በትር አድርጎ የሚጠቀመው የአብይ አህመድ ኦሮሙማ ቡድን ታዲዎስንና ሌሎቹን አሽቶ አሽቶ ሲበቃው ቢፈታቸው ብዙ ገንዘብ በዋስትና ስም ሊዘርፍ እንደሚችል ካለፉት ድርጊቶቹ መገመት አያቅትም።በኦነግ ኦሕዴድ ተላላኪ በሆነው በብአዴን በኩል በፋኖ ዘመነ ካሴም ልይ የሚሸረበው ሴራ ቀላል አይደለም።እሱም እንዲሁ በችሎት ቁማር ተጫዋቾች እዬተጉላላ ይገኛል።ከዚያም አልፎ ተርፎ ለኦነግ ገዳዮች አሳልፎ ለመስጠት ፍላጎት እንዳለ ሾልኮ የወጣው መረጃ ያረጋግጣል።

በዚሁ ህዳር ወር የአብይ አህመድ ሕገወጥ ቡድን ሽመልስ አብዲሳ በተባለው የክልሉ መሪ በኩል አዲስ አበባን ከጥቅም ውጭ እናደርጋታለን ባለው መሰረት አምስት የከተማዋን ዳርቻ ቦታዎች አንድ ላይ ሰብስቦ ሸገር በሚል መጠሪያ አዲስ ከተማ የመመሥረቱ ዕቅድ ይፋ አድርጓል።ይህንንና ሌሎቹንም የኦሮሚያ አገር ምስረታ እንቅስቃሴዎች የልማት ዘርፎች ናቸው ብለህ የምትጃጃል የአዲስ አበባ ነዋሪ

በቀጣዩ እርምጃ ከኦነግ ካራ ብትተርፍ የሚገጥምህ ጉሮሮህን ታንቀህ ከአዲስ አበባ መባረር እንደሚሆን ተረዳ።

በዚህ በያዝነው ህዳር ወር ያዬነውና እያዬነው ላለው ቀውስ ቀደም ሲል በሕዝብ ላይ እልቂት ያደረሰውን የህዳር ወረርሽኝ በሽታ ለማሶገድ የፈጠርነውን የእሳትና የጭስ ዘመቻ ብልሃት የሚመስል ዘዴ ተጠቅመን የሰፈነውን የጎሳ ፖለቲካ ወረርሽኝ ለማሶገድ የሚረዳንን አገር አቀፍ ሕዝባዊ እምቢተኝነት፣ መፍጠር ያስፈልጋል።ቀጣዩ የህዳር ወር ተመሳሳይ የመከራ ሸክምና ለእልቂት የምንዳረግበት ወቅት ሳይሆን በሰላም፣በእኩልነትና በአብሮነት ፣ለመኖር የምንበቃበት ካለፉት ህዳር ወራቶች የተለዩ እንዲሆንልን የትግል ችቦ ለመለኮስ ሁሉም አገር ወዳድ ሆ! ብሎ እንዲነሳ ደጋግመን ጥሪ እናደርጋለን።

በክህደትና በራስ ወዳድነት የተበከለው በሥልጣን ላይ ያለው የሌቦች ቡድን እርስ በራሱ እዬተባላ ንትርኩን ወደሕዝቡ ለማስተላለፍ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል።ላለፉት 32 ዓመታት ዬት ነህ ብሎ ያልጠዬቀውን ሕዝብ ሲመቸው መጠቀሚያ ሳይመቼው ምሽግና ዋሻ ለማድረግ ሲቅበዘበዝ ማዬቱ የሥርዓቱን መበስበስና መፈራረስ ያሳያል። ለዚህ ማስረጃው ሽታዬ ሽታዬ ሲባባሉ የቆዩትና ሕዝቡን ለመከራ በዳረጉት የኢሕአዴግ ብልጽግና ባለሥልጣኖች መካከል በጥቅምና ስልጣን ምክንያት የተነሳው የእርስ በርስ ንትርክና ግብግብ ውስጥ መግባት ነው።ለውዝግቡ መነሻ የሆነው የሕዝቡ በተለይም የአማራው ማህበረሰብ መነሳሳትና መነቃቃት መሆኑ በዋናነት ይቀርባል።በዚህ የተነሳ በአማራው የብልጽግና ክንፍ ውስጥ የመንገጫገጭ ብቻም ሳይሆን የመተራመስና እርስ በርሱ የመባላቱ ትዕይንት ገጦ ታይቷል።የአብይ ኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና ስብስብ ሌባን የማሶገድ ዘመቻ በሚለው ሽፋኑ ለአገዛዙ የማይመቹትን ብቻም ሳይሆን ሲያገለግሉት ኖረው ያረጁና ያፈጁ፣በሕዝቡም የተጠሉትን አሶግዶ በአዲስ ፈረሶች ለመተካት ያቀደው ስልት በሁሉም ዘንድ ብርክና ሽብር አስከትሏል።እንደ ደመቀ መኮንን የመሰሉት ኢጋሰሶች ከነበራቸው የባንዳ ወንበር ተስፈንጥረው አመድ ላይ መጣላቸው ይፋ ባይሆንም የሚነፍሰው ንፋስ ይናገራል።ይኸው ኢጋሰስ በወያኔና በኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና መካከል በደቡብ አፍሪካ ከተማ የተካሄደውን ድርድር በመንግሥት በኩል የተመደበውን ቡድን የመራ መሆኑ በአብይ አህመድ የተነገረውን በሚቀናቀን መልኩ እንኳንስ ቡድኑን ሊመራና የስምምነቱንም ውጤት እንደማያውቅና የሰማውም እንደ ማንኛውም ሰው በሚዲያ መሆኑን ይፋ አድርጓል። የስርዓቱን መበስበስ ለመረዳት ከዚህ የበለጠ ምን ማስረጃ ይመጣል? ለጸረ ኢትዮጵያ ቡድኖች ለሆኑት ለወያኔና ለኦነግ ካለው የረጅም ጊዜ አገልግሎትና የሥልጣን ቦታ አንጻር ደመቀን አነሳን እንጂ ሌሎችም ለብልጽግና መጠላት ምክንያት ይሆናሉ፣ወይም በመቃወም ያጋልጣሉ የሚባሉት ሁሉ እጣፈንታቸው ተመሳሳይ እንደሚሆን አያጠራጥርም። ለ32 ዓመት በአማራው ስም የሥርአቱ የጋሪ ፈረስ ሆኖ ሲያገለግል የነበረው ደመቀ መኮንን የተባለ ወንጀለኛ አሁን ያገልግሎት ዘመኑን ጨርሶ እንደ አገዳ ተመጦ መተፋቱን እራሱ ሳይቀር በተናገረው እኔ አላውቅም ማጋለጫው ይፋ አድርጓል።ከነበረው የምክትል ጠ/ሚኒስትርነት ቦታ ተወግዶ ከውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ለመሰናበት በር ላይ መቆሙን ሥራውን በሌላው ተረኛ በረዲዬዋን ሁሴን መቀማቱ ያረጋግጣል።

በሌላዋ ሌባ በአዲስ አበባ የለሚኩራ ክ/ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት የመሬት ጉዳይ ሃላፊ ሆና በሙስናና መሬት በመቸብቸብ ትታወቅ በነበረችው ላይም ክስ ሊመሰረትባት መሆኑ በወንጀል ሸርከኞቿ በኩል በደረሳት ያምልጭ ምክር ካገር ወጥታ ሰርቃ በቱርክ አገር በገዛችው ዘመናዊና ውድ መኖሪያ ቤት መኖር እንደጀመረች ይፋ ሆኗል። ይህች ሌባ ብትያዝ የስርቆት ገመዱ እነማን ድረስ እንደሚተረተር ስለሚታወቅ ያንን ለመከላከል ሲባል በመንግሥት ባለሥልጣኖች እውቅና እንድትወጣ መሆኑ በሚቆጣጠረው የአዬር መንገድ ኬላ በኩል ማለፏ ማስረጃ ነው።አብይ አህመድ ሌባዎችን ለማደን

የተነሳ በመምሰል በከፈተው ዘመቻ የተጋለጡትን ማሳደዱ እራሱን ነጻ ያደረገ ቢመስለውም አሳ ግማቱ ከጭንቅላቱ ነውና ባባከነው በቢሊዮን የሚቆጠር ዶላርና ለሥልጣኑ ሲል ከወያኔ ጋር ጦርነት ከፍቶ በመቶ ሽ ዎች ለጠፋው ሕይወትና ለወደመው ንብረት፣አሁንም በዬቦታው ለሚከናወነው የአማራው እልቂት አንድ ቁጥር ተጠያቂ ነው።

በዚሁ ባልተገባደደው ህዳር ወር ከታዘብናቸው ውስጥ የኦሮሙማው የመከላከያ ክንፍ ማን አለብኝነትን የሚያጸና ሕግ አርቅቆ ለሚቆጣጠረው ለሕዝብ ምክር ቤት(ፓርላማ)ማቅረቡ አንዱ ነው። በጦር ሃይሎች አዛዥ በአብይ አህመድና በተባባሪው በብርሃኑ ጁላ የረቀቀው ይህ አንቀጽ በጦርነት ጊዜ በሽብርና በሕገወጥ ተግባር ላይ የተሰማሩትን ወንጀለኞች ለመቅጣት በሚል ሽፋን ተቃዋሚና ለመብት የሚታገሉትን ሁሉ በአንድ ቋት ውስጥ ከቶ ለመቅጣት የተሰናዳ የበቀል አንቀጽ ለመሆኑ የሕግን ትርጉም የሚያውቅ ብቻ ሳይሆን  የአካባ አሕዴድ ብልጽግናን መሰሪነት የተረዳ የሚገነዘበው ነው።እንደ ዓለም አቀፉ የወታደር ፍርድ ቤት አሰራር ከሆነ በጦርነት ጊዜ  ሚስጥር  አሾልከው ለጠላት ወገን የሰጡ፣ከፍላቸውን ከድተው ከጠላት ጋር የተቀላቀሉ፣ለወገን ጦር የተሳሳተ መረጃና አመራር በመስጠት ለጉዳት የዳረጉ፣ ለጠላት ማሸነፍ ምክንያት የሆኑ፣የጦሩን ስንቅና ትጥቅ በመሸጥና በመዝረፍ ለግል ጥቅማቸው ያዋሉ፣በሲቪል ማህበረሰብ ላይ ኢሰብአዊ ድርጊት የፈጸሙ ፣በአጠቃላይ ከወታደራዊ ስነምግባርና ከጦርነት ደንብ የወጣ ድርጊት የፈጸሙ የሚቀጡበት ችሎት ነው።የአብይና የብርሃኑ ጁላ የጦር ፍርድ ቤት እንዲመለከተው ያረቀቁት አንቀጽ ግን በሲቪሉ ማህበረሰብ በኩል የሚነሳውን ተቃውሞና የትግል እንቅስቃሴ ለመቅጨት ሲባል የትግሉ መሪ ናቸው በሚሏቸውና ለዘረጉት የኦሮሙማ ፖለቲካና ዓላማ እንቅፋት ሊሆን የሚችለውን የማህበረሰብ ክፍል ለማጥቃት የሚያስችላቸው አንቀጽ በሚቆጣጠሩት ፓርላማ በሚሉት የጎሰኞች በረት በኩል ሕጋዊ እውቅና እንዲያገኝ ያደረጉት ሕገወጥ አካሄድ ነው። ይህ አካሄድ ተግባራዊ ከሆነ የፍርድ ሂደቱ በወታደር ችሎት የሚከናወን ከሆነ ያልታወጀ ወታደራዊ አምባገነን  መንግሥት ያገሪቱን ሥልጣን ተቆጣጥሮታል  ማለት ነው።

ሌላው ይሉኝታ ቢስ የፕሮፓጋንዳው ዘመቻ የተከፈተበትንም ጉዳይ ታዝበናል። በግብጽ በሻርም አልሸኽ የቱሪስት መናኸሪያ በሆነችው ከተማ በተደረገው የዓለም አቀፍ የአዬር ለውጥ(Climate Change) ጉባኤ ባሳለፈው ውሳኔ ለአፍሪካና ለመሳሰሉት አገሮች መቋቋሚያ ከምዕራብ አገሮች ከተመደበው ገንዘብ ኢትዮጵያ $50ሚሊዮን ዶላር ለማግኘት የቻለችበትን አጋጣሚ በሚመለከተው ዙሪያ ነው።ይህንን የበጎ አድራጎት ይሁን የግዴታ ውል ማስፈጸሚያ ገንዘብ ድርሻ አብይ አህመድ በበሳል አይምሮው ባደረገው ክርክሩ እረቶ(አሸንፎ) ያመጣው ሽልማት አድርገው የሚያናፉ ውታፍ ነቃይ የሚድያ ዘርፎች ሲያስተጋቡ ሰምተናል።ያም ሆነ ይህ ልብ ወለድ ፕሮፓጋንዳ  እውነቱን የሚቀይር ስላልሆነ ይብላኝ ለናንተ ብለን አልፈናቸዋል። ይህ ማለት ግን በታሪክ የሚጠዬቁበትን ዶሴ ከማዘጋጀትና ከመጠበቅ እንቆጠባለን ማለት አይደለም።ሁሉም በሥራው የተከፈተበት ዶሴ መኖሩን ይወቀው እንላለን።ገሎ፣ዘርፎ፣ሰርቆ፣ ዋሽቶ፣በህዝብ ላይ አላግጦና፣ለወንጀለኞች ምርኩዝና  ደጋፊ ሆኖ የተጠቀመ  የሚጠዬቅበት ጊዜ እሩቅ አይሆንም፣አወናብዶ መኖር የሚቻልበት ጊዜና ዕድሉ የመነመነ ነው።የጊዜ ጉዳይ ነው ሁሉም የሥራውን ያገኛል።

የትግሉ እሳት ይቀጣጠል፤የፋኖ አንድነት ግንባር  ይጠናከር!

በአገር ውስጥና በውጭ አገር ያለው  የጎሳ ፖለቲካን የሚቃወም፣ለአገር አንድነት፣ ለዴሞክራሲ፣ ለእኩልነትና ለፍትሕ የቆመው  በአንድ ግንባር ስር ይሰለፍ!!

ኢትዮጵያ በአንድነትና በነጻነት ለዘለዓለም ትኑር!!!